

# በቶሮንቶና አካባቢው ለምትገኙ ኢትዮጵያውያን በሙሉ

አገራችንን ኢትዮጵያን ላለፉት ሃያ ዓመታት በዘርና በቋንቋ ከፋፍሎ በአምባገነንነት ሲገዛ የቆየው የወያኔ ኢህአዴግ አገዛዝ ይህን የጥፋት ጉዞውን በመቀጠል ላይ እያለ፣ በሰሜን አፍሪካና በመካከለኛው ምሥራቅ እየተካሄደ ያለው የለውጥ ማዕበል ወደ ኢትዮጵያም መድረሱ እንደማይቀር ስላስፈራው ባለሥልጣኖቹን፣ ጥቂት ደጋፊዎቹንና ካድሬዎቹን በማሰማራት በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን ለማዘናጋትና ለመከፋፈል "ለሀገራችን ልማትና እድገት ህዝባዊ ስብሰባ" በሚል ሽፋን በአሜሪካና በካናዳ ትላልቅ ከተሞች በኤምባሲ ሰራተኞቹ አስተናጋጅነት በማሰማራት ኢትዮጵያዊው በአንድነት ድምጹንና ድጋፉና በገዛ አገሩ መከራውን፣ ችግሩን፣ እስራቱን፣ ግድያውን፣ ርሃቡን መንገላታቱ ለበዛበትና በቃኝ መረረኝ ብሎ ለሚነሳው ሕዝባችን እንዳይሰጥና እንዳያሰማ ለማድረግ አሰቀድሞ የቀየሰው ሴራና ተንኮል በአንዳንድ የአሜሪካ ከተሞች እየተጋለጠና እየከሸፈ ሲሆን ወደ ካናዳም **ቶሮንቶና ኦታዋ በኤፕሪል 9 እና 10/ 2011** ዓ/ም መታሰቡን ደርሰንበታል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በታሪካችን ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ መልኩ በከፍተኛ የኑሮ ውድነት የተነሳ በልቶ ማደር ብርቅ እየሆነ በመጣበት፣ አፈናና ጭቆናው በከፋበት፣ አርሶ አደሩ እየተፈናቀለ ለውጭ አገር ከበርቴዎች መሬቱና ለሃምሳና ዘጠና ዘጠኝ ዐመት በሊዝ እየቸበቸበ ባገሩ ባይተዋርና ተፈናቃይ ሆኖ በረሃብ ሲገረፍና በእጅ አዙር የቅኝ ግዛት ወጥመድ ውስጥ እየጨመረው ሳለ ኢትዮጵያ አደገች ለማች እያለ እየቀላመደ ተባባሪና ደጋፊ ሆድ አደር ፍለጋ መሰማራቱን አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊው እጁና አጣጥፎና ችላ ብሎ የማይቀመጥና የማይመለከት መሆኑን ለማሳየት ዝግጁ ነው።

በቅርቡ የተቃውሞ ድምጻችንን በጋራና በአንድነት ሆነን በቶሮንቶ ከተማ ስለምናሰማ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ቀኑን፣ ቦታውንና ሰአቱን በንቃት እንድትጠባበቁ በወገናችን ስም ጥሪያችን እናቀርባለን።

ተቆርቋሪ ኢትዮጵያውያን በቶሮንቶ